# የኮሮናቫይረስ ምልክቶች (COVID-19)

## የሚከተሉትን ሊያካትት የሚችለውን የ COVID-19 ምልክቶች ይወቁ፡



ሳል፣ የትንፋሽ መቆራረጥ ወይም የመተንፈስ ችግር



ትኩሳት ወይም ብርድ ብርድ ማለት



የጡንቻ ወይም የሰውነት ሕመም



ማስታወክ ወይም ተቅማጥ



ከዚህ በፊት ያልታየ የመቅመስ ወይም የማሽተት ስሜት ማጣት

ምልክቶቹ ከመለስተኛ እስከ ከባድ ሕመም ሊደርሱና COVID-19 ለሚያስከትለው ቫይረስ ከተጋለጡ ከ 2-14 ቀናት በኋላ ሊታዩ ይችላሉ።

### አንድ ሰው የ COVID-19 ድንገተኛ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ካጋጠመው ወዲያውኑ የሕክምና እርዳታ ይፈልጉ።

- የመተንፈስ ችግር
- በደረት ላይ የማያቋርጥ ህመም ወይም ግፊት
- ከዚህ በፊት ያልታየ ግራ መጋባት
- ለመንቃት ወይም ነቅቶ ለመቆየት አለመቻል
- የፊት ወይም የከንፈሮች መገርጣት

ይህ ዝርዝር ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ምልክቶች ሁሉ ያካተተ አይደለም። ለእርስዎ ከባድ ወይም አሳሳቢ ለሆኑ ማንኛውም ሌሎች ምልክቶች እባክዎ ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ይደውሉ።

Centers for Disease Control and Prevention
National Center for Emerging and Zoonotic Infectious Diseases

cdc.gov/coronavirus

CS-317142-H